# የላካኒያን ሳይኮአናሊሲስ እና መረቅ

*Teshale Kebede Bedriya*

በእርግጥ "መረቅ " በኪነ ጥበብ ምትሃት ፣ በእሳቤ ጥራትና በፍልስፍናው ጥልቀት በከባዱ የሚያነቃንቅ ብሉይ ስራ ነው።

እውቁ ፈረንሳዊው የሳይኮአናሊሲስ ጠበብት ዣክ ላካን፣ ሳይኮአናሊሲስ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ የፈጠረ ፈላስፋ ነው። ፍሩድን በጥልቀት ያጠናና በስራዎቹም ሥነ - ፅሁፍን ፣ ፊልም ፣ ፖለቲካና በማህበረሰብ ጥናት ላይ ተጽዕኖውን ማሳረፍ የቻለ አሳቢ ነው። እንደ ላካን እሳቤ "ሰው " በዋናነት የህይውት ዘይቤው የተበጀውና መንገዱን የተቀየሰለት ቋንቋን መጠቀም ከጀመረበት ቅፅበት ጀምሮ በሚገነባው ኢ-ንቁ የአዕምሮው ክፍል ነው :: ይህም “Unconscious mind is structured like a language” ይላል።

የላካንያን ኢንቁ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ትዕምርቶችና መዋቅሮች ማከናወኛ (ሚዲየም፣ ስቴጅ) ጭምር ነው።

በዋናነት አንድ ህፃናን ከተወለደ በኋላ ራሱን የሚያውቀው በእናቱ ጡት አማካይነት ነው። በዚህ ጊዜ ጨቅላው እራሱን መለየት አይችልም፤ ይልቁን ፍፁም እርሱነቱንና አካባቢውን ማገናዘብ ባልቻለበትና እራሱን በእናቱ የመስለባቸውን ደረጃዎች ያልፋል ::

ጨቅላው ከእናቱ ጡት እንደተነጠለ (ከ6 እስከ 18 ወራት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል) የእኔነት ምስሉን መቅረጽ ይጀምራል። የእናቱ አንድ አካል እንዳልሆነም ይረዳል። ይህን ego form የሚያደርግበት እርከን ላካን Imaginary order ሲል ሰይሞታል።

ይህን imaginary order በማለፍ በትዕምርትና በቋንቋ ወደተዋቀረው ስርዓት ውስጥ የሚገባው ጨቅላው እናቱም ብትሆን ከሙሉ እሱነቱ የተነጠለች (M)Other እንደሆነች ይረዳል።

ሕጻኑም የደስታና የእርካታ ምንጩን ትቶ በማህበረሰቡ አስቀድሞ ወደተሰሩት ፍላጎቶች ፊቱን ያዞራል። (unreplaceable lack) በሌላ አገላለጽ ህፃኑ ተፈጥሯዊ ፍላጎቱ ፋንታሲ ወደ ፋንታሲ ሽግግር ያደርጋል ::
በዚህም ህጻኑ ከተፈጥሯዊ እሱነቱ ወጥቶ በቋንቋና በትምዕርት ወደ ተዋቀረው ስርዓት ውስጥ ይገባል። ይህንን የቋንቋ ስርዓት በአርስቶትል አባባል ... “Automation:-Signifiers of the signifiers) ነው። ይህም ተፈጥሮአዊ እሱነቱና እርካታውን ሙሉ በሙሉ የሚያጣበትና የሌሎች ፍላጎት (desires of the Other) ለተፈጥሯዊው ፍላጎቱ አማራጭ ሆኖ የሚመጣበት ነው።

ስለዚህ የላካንያን ሳይኮአናሊሲስ መሰረት የሆኑት ሶስቱ እርከኖች ማለትም Imaginary፣ Symbolic እና Real order፣ ለትዕምርታዊ ዓለም ተገዢ ይሆናሉ:: በዚህም ተፈጥራዊ እውነት (real) ሙሉ በሙሉ በቋንቋ ስለ ማይወከል ከቋንቋ ውጪ ይሆናሉ ፤ ይህንን ለካን (Symbolic castration) ይለዋላል ::
በዚህ በቋንቋ የሚመራው ግለሰብ እነዚህን ጉዳዮች በሌላ ማህበሰባዊ እውነታ (social reality) ይተካሉ :: ስለዚህም ተፈጥራዊው እውነት እና እርካታው (enjoyment) ፣ ስነ-ልቦናዊ ምስቅልቅሎሽ (trauma)

በመሆን ወደሌላ ምናባዊ አለም ወይም ፋንታሲ ሽግግር (transference) ያደርጋሉ። በዚህም ተፈጥራዊ እውነታ እና እርካታ ፋንታሲ ውስጥ ይገባሉ ::

በዚህም መሰረት መረቅን በላካን ለማንበብ የተደረገውን ጥረት እንይ ፦

"ከሁሉ ለመሸሽ የምችል ዓይነት ወደ አማን ደረት ተጣበቅሁ። አማን ጓደኛዬ ነው ፣ ጓደኛዬ ነበር፣ እና ምን አለበት? አይኖቼን ገርበብ አድርጌ አላዛርን አስባለሁ። አላዛር አ አይኖቹን ጨፍኖ እየተልቆሰቆሰ ሲያቅፈኝ። በፀሃያማ ቀን በቀስታ ታኮኝ ሲቆም። በሃሳቤ እዛና እዛ ስቀባዥር አማን አናቴን ሲስመኝ ሰማሁት :: አላዛርን ማለም አቆምኩ :: ግራ በመጋባት ምልከት ቀና ብዬ አየሁት :: ቀና ብዬ እያየሁት ሳለሁ ሳልጠብቀው አፌ ላይ ሙሉ በሙሉ ሳመኝ። በፍጥነት ከእቅፉ ተላቀቅሁና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ቆም ብዬ ጃኬቴንና ሱሪዬ አስተካከልኩ።

" የት ነው? "አለኝ
"ቤት ለመሄድ ነበር "ተራዬ እንዳልሆነ አውቃለሁ
" መኪና የለም ::ትንሽ ረጋ በይ :: ተራሽ ገና ነው"
የምመልሰው አልነበረኝም .....

ይህ ሁነት በመጋቢት 1969 ተባረኪ የወጣቶች ሊግ ሰላማዊ ሰልፍ በተደረገበት ሌሊት ነው። በመጀመሪያ ተባረኪ ሰላማዊ ሰልፉን ለመሳተፍ ፈርታ ስታመነታ ነበር። ሆኖም ፍራቻዋን ለትግል አጋሯ አማን (የእሷም ፣ የአላዘርም አብሮ አደግ) በቁንጽል ወይም በዝርዝር አትነግረውም፡፡ " ፈሪው ወዳጄ አላዛር በልቤ ጥርጣሬ አስገብቶ ሳይሆን ይቀራል ፤ ለአማን ልነግረው አልደፈርኩም። ግን ደግሞ የጠላቴን አይን እያየሁ ግንባሩ ላይ መጮህ እፈልጋለሁ ..." (መረቅ ፥ 246።)

ከትዕምርታዊ ስርዓት ይልቅ ፣ ነገሩን በቀጥታ ለማየት ከፈለግን ተፈጥሯዊው ፍላጎት እንደሆነ እንረዳለን። ነገር ግን ይህ ተፈጥሯዊ ፍላጎት ለማግኘት ለአማን የሚቻል አይደለም ፤ ይህም የአማን ፍላጎት ወደ ፋንታሲ ውስጥ ተሻጋሪ ይሆናል። በመሆኑም አማን ተባረኪ የዓላዛር ፍቅረኛ መሆኗ እያወቀ እሷን ከመመኘት አላገደውም፤ ይህም ተፈጥሯዊ ፍላጐቱ ለማርካት የነበረውን ማንኛውም አጋጣሚ ከመሞከር ወደኋላ አላለም ፤ ይህም ተባረኪ በአማን አዕምሮ ውስጥ የምትንሳፈፍ ለተፈጥሮኣዊ ፍላጎቱ መልስ ሰጪ ናትና። እዚህ ጋር የስሎቮን ዢዤክን ሀሳብ ላምጣ ፦ "For a Man ,the relationship with a women is possible only in as much as she fits his formula " ይላል ::

ለዚህም አካላዊ ባይሆንም በፖለቲካው መድረክ የነበራቸው ግንኙነት ለዚህ ወሲባዊ ፍላጎት ልዋጭ ሆኖ መቅረቡን እናያለን። እንዲህ ትላለች ቴቤ ፦

" ....አማንን ሩካቤ ስጋ እምቢ ብላውም ባማረ መልክ በፖለቲካ ተራክበናል። እኔ እንደማልረሳው እሱም አይረሳኝም " ትላለች (መረቅ፥293) ።

..ሌላ እንጥቀስ ...
" የሰላማዊ ሰልፉ ማግስት በመሸሽ ላይ እያለሁ ፣ ትዝ ያለኝ ብቸኛ እናቴና አላዛር ነበሩ። ለብቻዬ በኮሮኮንች ላይ እየተወለካከፍኩ ስሮጥ የከበበኝ ጨለማ ማሃል የታወሱኝ እማማና አላዛር ነበሩ። ፍቅር ከዋናው አላማዬ በላይ የሚንሳፈፍ ጉድ የለዉም (መረቅ ፥ 246)"

እዚህ ጋር ተባረኪ ፣ እናቷና ዓላዛር ተያይዘው የመጡት ሁለቱም ለተፈጥሯዊ ፍላጎቷ መገኛ ቢሆኑም የነበረችው በትርክት ውስጥ ስለሆነ አታገኛቸውም። ምክንያቱም ትዕምርታዊ አለም ተፈጥሮአዊ እዉነት (real) እርካታ (jouissance) በቋንቋ አይወከሉም ፤ ይህም እንዴት ወደ ፋንታሲ ሽግግር እንደሚደርግ ከላይ አይተናል።

ይህንን ክፍተት በፋንታሲ ከተያዘ በኋላ ለሌሎች ፍላጐት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ፤ በዘመኑ የነበረው ፋንታሲ ውስጥ መጫወት የሚችል ርዕዮት ዓለም ደግሞ ማርክሲዝምና ሌኒንዝም ነው፡ ፡ በመሆኑም የማርክስ ርዕዮት ዓለም የእናቷና የዓላዛር ተቀናቃኝ ሆኖ ይመጣል።

ዢዤክ እንደሚለው (fantasy is narative) ፋንታሲ ትርክት በመሆኑ በወቅቱ የነበረው የማርክሲስም ርዕዮተ አለም አዕምሮዋን መቆጣጠር መቻሉና አዕምሮዋ ውስጥ ያለዉ የፋንታሲ መዋቅር ወዲህ በእናቷና ዓላዛር እሳቤ ወዲያ በርዕዮተ ዓለሙ ለሁለት ተከፍሎ እናያለን።

....እንጨምር ...

"ተባረኪ ችግሩ አላዛር ከታሪክ ዉጭ ሆኖ ነው የሚያየኝ። እኔ ደግሞ ታሪክ ልስራ እየለፋሁ ነው። ጊዜዬን ለጭቁን ህዝቦች ነፃ መውጣት መስጠት ነበረብኝ። ለምወደው ድርጅቴ መስጠት ነበረብኝ " አዳም ፣ 242) :: በመሆኑም አላዛር ለተባረኪ የማይደፍር " ፈሪ" ወይም የማይገባው " ደደብ " ወይም " ከግል ስሜቱ መውጣት የከበደው ራስ ወዳድ ነው" (መረቅ ፣ 240)

" አማን በአዕምሮዬ መጣ :: አላዛር የሆነ ሴታ ሴት መሰለኝ። የሆነ ያልወለደኝ እማማ :: ጡት ባያጠባኝም የሆነ የወለደኝ ምንትስ። የምወደውን ልጅ ስሮጥና ስሸሽ አስታውሼው ፣ ስረጋጋ ፣ በዝምታ በልቤ እንዲህ አልኩት ፣ ማዘሬ ነህ ምንድነህ ?" (መረቅ ፣ 248)።

በላካናውያን እሳቤ ተፈጥሯዊው እውነት ትራውማ ነው እንጂ በትዕምርታዊ እርከን ዉስጥ ያለ ነገር አይደለም :: ለዚህም ነው ፋንታሲ ይህንን ትራውማ ለማከም ለሚደረገውን ጥረት መድረክ ሆኖ ብቅ የሚለው (fantasy is a setup) ::

ይህ የእሷ እጣ ፈንታ ብቻ አይደለም ፤ በዘመኑ የነበሩ ወጣቶች ጣጣ ነው፤ ይህም ወጣቶቹ የወል ልቦናን ገንብተው የወል እርካታን ለመገንባትና ለማግኘት የሚዳክሩት ፣ በዢዤክ እሳቤ (Collective jouissance) ዉስጥ የሚታይ ነው :: ስሎቬኒያዊው ስሎቮን ዢዤክ እንዲህ ይላል፡-

Nationalism thus becomes 'the privileged domain of the eruption of enjoyment into the social field.' The 'national Cause' is then cleverly related to Lacan's concept of 'the Thing', which is closely linked with the concept of jouissance; it is itself a materialization of jouissance.

እንደውም ብሔርተኝት ፣ ፋሺዝም ፣ ናዚዝምና ሌሎችም በዚህ በ Collective jouissance ውስጥ የሚታዩ ናቸዉ ይላል ::

ይህም በረቀቀ መንገድ የሌሎችን ወሲባዊ እርካታን ቀንብበው ለዓላማቸው የሚያውሉ ደስታ ስራቂዎች (ብልጦች) አሉ ይለናል :-

"What is at stake in ethnic tensions is always the possession of the national Thing: the ‘other’ wants to steal our enjoyment (by ruining our ‘way of life’) and/or it has access to some secret, perverse enjoyment. In short, what gets on our nerves, what really bothers us about the ‘other,’ is the peculiar way he organizes his enjoyment. In short, what gets on our nerves, what really bothers us about the ‘other,’ is the peculiar way he organizes his enjoyment. ( Slavoj Žižek ፥ 22) "

ይህንን ሃሳብ በሜሎስ ነቅናቂ እሳቤ እናጠናክረው :
“ ወሲብ ትልቅ ጉልበት ነው የወሲብን ስልጣን ወጣቶች ልብ ውስጥ እንይወጣ አድርገህ አምቀህ ለጫጫታ ትጠቀምበታለህ። በየአቅጣጫው ታፍነውና አንድ የፖለቲካ መውጫ ብቻ ቀዳዳ ካበጀህለት ባሪያ አገኘህ ማለት ነው “ (መረቅ፥162)

እዚህ ጋር በተለይ ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፣ መረቅና የስንብት ቀለማት ረቂቅ በሆኑ የስነ ልቦና ፤ የታሪክ፣ የፖለቲካ ፣ የማህበረሰብ እሳቤዎችና እጅግ በላቀ እና በተዋጣለት ኪነጥበባዊ አለም ውስጥ የተሰሩ ናቸው ::

በመሆኑ እነዚህ ብሉይ (Classic) ስራዎች በላካንያን እሳቤ በዋነኛነት በ " fantasy Structure ፣ desire እና Collective Jouissance " ውስጥ ለመተንተን ሁነኛ ማዕቀፎች መሆን ይችላሉ። ይህም አዳም ረቂቅ ፈላስፋና አሳቢ፣ ጥልቅ አንባቢና የተዋጣለት ደራሲ መሆኑን ከስራዎቹ መረዳት ይቻላል ::

***

ይህ ፅሁፍ ይድነቃቸው ሰለሞን (Ph.D) ለኢትዮጲስ ጋዜጣ ፣ ጥቅምት 11 ቀን 2011 ዓ.ም በወጣው ፅሁፍ ገፋፊነት ምክንያት የተፃፈ ነው። በዚህም የእሱ ፅሁፍ የተሳሳታቸውን ወሳኝ ጉዳዮች ለማረም ያለመ ነው። ለዚህም ሲባል የእሱን ቴክስቶች (ከመረቅ የወሰዳቸውን ተጠቅሚያለሁ) ለንፅፅር እዲመች :: ለተጨማሪ ንባብ ምክንያት ስለሆንከኝ ምስጋና ይድረስህ ::